# አኬልዳማን ማዜሙ ያብቃ!

ቢንያም ግዛው



ያ መሬት የጥፋት ፣ የሞት፣ የሀዘን ፣የደም ነውና አኬልዳማ ተባለ። የደም ምድር ማለት ነው። አሁንም የሰው ደም መፈሰሱ ቀጥሏል ። የግፍ እና የጭቆና ፣ የሰቆቃው ድምፅ ተሰተጋብቷል ። የህዝብ ሀዘኑ ገንፍሎሏል። ህዝባዊ የሆነ የይፈረድልን ድምፅ በሀገሪቷ ላይ እያስተጋባ ነው። ቀፎው እንደተነካ ንብ በቁጭት የተነሳው ዜጋ ምንም እንኳን ገዢው ቡድን ሊያፅናናው የሚችልበት እንቅስቃሴ ከቶ ባይኖረውም፥ እስከ ራማ የሚሰማ የለቅሶ ድምፁ በአለምም ሁሉ የሚስተጋባ ሆኗል። የ28 ኢትዮጵያውያን ህይወት በግፍ መቀጠፍ የሁላችንችንንም ልብ በአንድነት የሚሰበስብ እና ተከማችተን ክንዳችንን በሁሉ አቅጣጫ በማስተባበር ህዝባዊ የሆነ ዲሞክራሲያዊነትን የተላበሰ መንግስት እንዲኖረን ትግላችንን በማጠናከር ለህዝብ ያልቆመውን የወያኔን አገዛዝ ለማውደም ተማሪው፣ ሰራተኛው፣ አዛውንቱ ፣ ወጣቱ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሳውዲአረቢያውን ፣ የየመኑን ፣ የደቡብ አፍሪካውን ግፍ ተመልክቶ ምንም አይነት ህዝብን ሊያረጋጋ እና ሊፈውስ የሚችል ተግባር የሌለውን አረመኔ መሪ በህዝባዊነት በማመፅ እና ኢትዮጵያዊ መብትን ለማስከበር ብሎም ስልጣን የህዝብ እንዲሆን የአስተዳደሩን ዙፋን ከወያኔ በህዝብ እንቢተኝነት የሚነጠቅበት ሰአቱ ከምንግዜውም ይልቅ አሁን እነሆ ቅርብ ሆኗል።

በጎሳ፣ በብሔር፣ በክልል የመነታረኩን ነቀርሳ ወደጎን በመተው በወያኔ ላይ የማይቀረውን እና ውጤታማ ሊሆን የሚችለውን `` ሕዝባዊ ዓመፅ `` ከመቼውም በላይ ተግባራዊ ማድረጉ አማራጭ የማይገኝለት ምርጫ ሆኗል። ነውም። ሕዝቡ ምሬቱን አምቆ በልቡ ይዞት እና እንዲሁም በአገዛዙ አረመኔያዊነት ታላቅ ብስጭት ውስጥ የተነከሩት የራሱ የወያኔ አባላቶቹ እንኳን ጭቆናው እና ኢሰባዊነቱ ነፍሳቸውን አስጨንቆት፥ ልባቸው እየካደ ፤ በአመፅ የሚነሳውን ህዝብ ለመከተል ያቆበቆቡበት ዘመን ላይ መድረሳቸውን ወያኔ ውስጡ የተቦረቦረ የምስጥ እንጨት መሆኑን በጉልህ ያሳየናል። አገዛዙም ከድጡ ወደማጡ እያሽቀለቀለ መዳከሙን ይመሰክራል።

በሊቢያ ስለ ታረዱት ሰዎች ኢትዮጵያዊያን ስለመሆናቸው ምንም መረጃ የለኝም ብሎ ወያኔ ሊደባበቅ ቢሞክርም ፥ በግብፅ ያለውም የወያኔ ኤምባሲ ለዶክተር ተብዬው ወገኛ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ቴዎድሮስ አድህኖም ባቀበለው መረጃ ፥ ልብን ሊያሳዝን በሚችል መልኩ በቁስል ላይ እንጨት ስደድብድት እንዲሉ ፥ ከአንድ ከፍተኛ የሀገር ባለስልጣን የማይጠበቅ ንግግር ተስምቶ ሳያብቃ ፥ በዱር በገደሉ ተንጠላጥለው በብዙ መከራ ሊቢያ የከተሙትን ዜጎች በፈቃደኝነት ወደ ሀገራቸው መመለስ የሚፈልጉ ቢገኙ፥ ግብፅ ካለው ኤንባሲ ጋር ግንኙነት እንዲያደርጉ የሚል ሌላ ልብ አሳዛኝ ወሬ አውርቷል ። በእርግጥ ነገ ምን ሊገጥመው እንደሚችል የማያውቅ ስደተኛ በተንቀራፈፈ እና የተቀላጠፈ ስራ ሳይኖረው በሙስና እና በዘረኝነት ከተቀፈደደ ኤንባሲ ጋር በምን ፍጥነት እና ኢኮኖሚው ነው ስደተኛው ለመመለስ ካይሮ ካለ የወያኔ ኤምባሲ ጋር ግኑኝነት የሚፈጥረው? የሚያመለክተው? ቢመለስስ ምን ሊጠብቀው ነው? ያው ሀገራቸውን ጥለው የሄዱ ምሳቸውን አግኝተው ተመለሱ ከማለት ሌላ ምንም ሊደሰኩር አይጠበቅም።

ከዚህ በመነሳትም ዜጋው ከገባበት አረንቋ ማጥ ማምለጥ የሚችልበትን ዘዴ እንደመንግስት ሊቀየስ የተገባው መፍትሔ በርግጥ ይህ መሆኑ ሀዘናችንን እጥፍ ድርብ አድርጎታል። ይህ ልብን የሚያሳዝን የወያኔ ምልከታ ምን ያህል ለኢትዮጵያዊያን ደም መፍሰስ ልቡ እንደማይደነግጥ እና በደቡብ አፍሪቃም በየመንም አልፎም ተርፎ ከተኩል ሰአታት በላይ በተጨባጭ ፊልም ተደግፎ የታየ ሆኖ ሳለ በተለያዩ የዜና ምንጮች ላይ የተዘገበውን የሊቢያውን አሰቃቂ ግድያ ገና እያተጣራሁት ነው በማለት በራሱ የዜና አውታር መዘገቡ ወያኔ ፍፁም የሆነ እንቅልፍ ውድቀበት እያንጎላጀጀው መሆኑን ያጠይቃል። እጅግም አሳፋሪ ከመሁኑም በላይ ዜጋው ደራሽ እና መከታ እንደሌለው በተጨባጭ የሚያስረዳ ሁኔታ ነው ።

ነገር ግን እንደ ኢትዮጵያዊነታችን የምንረዳው ተጨባጩ ጉዳይ በወጣቶቹ ላይ የሚያታው የጠነከረ ግንባር የጅግና ልጆች መሆናችውን እና በለበሱት ፀጋ ሞት ወደነርሱ ሊመጣ አንድ ስንዝር ቀርቶት፥ ቢላቸው እየተሳለ እና ክላሹ ተቀባብሎ እየሰሙት ለመጨረሻ ጊዜ መሞታቸው ካልቀረ እግር ልሳም፣ ልለማመጥ፣ክጄ ላምልጥ አላሉም ። ምንም እንኳን ወያኔ ማንነታችውን ለማረጋገጥ የልደት የምስክር ወረቀት ይገላበጥ ፥ ይጣራ ፥ ብሎ በቅጡ ያላስቀመጠውን ዶሴ ሊያገላብጥ ፊቱን ቢደብቅም ፥ ይህ የማይቀየር ኢትዮጵያዊ ወኔ እና ሞትን ለመጋፈጥ በኩራት ሳይልመጠመጡ ክብርን ጠብቆ ወደ ሞት መጓዝ የአፍሪቃ ቀንድ ልጆች ኢትዮጵያዊያን መሆናቸውን የግንባራቸው መልክ ያመላክተናል።

የማይፈራ፣ ለመታረድ እየተጋዘ፥ ኩሩ የሆነ ወጣት ህዝብ፥ ትናንት የነበረው ፥ተጨባጭ ለውጥን ለኢትዮጵያ ያመጣው የወጣቱ አስገምጋሚ ቁጣ፥ የንጉሱ በትረ መንግስት ያብቃ፣ እያለ የለውጡን ትግል ያፋፋመው በተለይም ወጣቱ ክፍል ጠንካራ በሆነ እና በተደራጀ ኃይል ሲነሳ ፣ታሪክ ሊለውጥ እንደሚችል በአፄው ዘመን የነበረው የየካቲቱ ህዝባዊ አመፅ ያመጣው ታላቅ ለውጥ ተመክሮ ይሆነናል። ኢትዮጵያዊ ወጣት ልበ ሙሉ ነው። አይፈራም ፣ አይለማመጥም፥ ሲደራጅ ህይወቱን በፈገግታ ይገብራል።

ከጠላቱ ምህረትን ሳይለምን በደሙ የትግሉንም የእምነቱንም ታሪክ ፅፎ ሲዘከር ይኖራል። ወያኔ ራሱም ቢሆን ይህን የታሪክ ማህደር በሚገባ ያውቀዋል። የሚበረግግለትም ትግል ይኸው የተባበረውን የወጣቱን አመፅ መሆኑ ግልፅ ነው። ኢትዮጵያዊው ወጣት ካበረ ከተባበረ ለሞት እንደማይተኛ የታወቀ ሀቅ ነው።

ዛሬ በአገራችን እስካሁን ካደረሰው በላይ ጥፋት ሊያደርስ ብቃት ያለው ጨቋኙ ገዢ የስልጣን ባለቤት ሆኖ ሳይፈይድልን ከኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ ተቀምጦ በየክፍለሀገራቱም ሆነ በውጭ ሀገር በሚገኙት ወገኖቻችን ላይ በሚደርሰው ግፍ የዜጋው ደም ፈሶ ሲቀር እና ደመ ከልብ ሲሆን ወያኔ ግን ባላየ ባልሰማ፣ ጆሮውንም ፣ ልሳኑንንም፣ አይኑንም፣ ጠርቅሞ ጉዴን ደብቁልኝ! ቢልም እንኳን ኢትዮጵያዊው ቀርቶ ሌሎችም ቢሆኑ እውነቱን በማራገብ ላይ ተሰማርተዋል ።

በተለያየ አቅጣጫ እና በር ከ80 ቹ ዓ.ም ወዲህ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ተሰደዋል። በሊቢያም ይህን የመሰለ ግፍ ተቋድሰው ሲልም ደግም ከእንዲህ አይነቱ ጭካኔ በስንት ድብብቆሽ ደግሞ አልፈው ወደ አውሮጳ ለመቀላቀል አደገኛውን የቀይ ባህር በትናንሽ ጀልባዎች ታጭቀው የጨካኝ አሸጋጋሪ ደላሎችን ግፍ የተሞላበት እርምጃ በመቋቋም የማይጨበጠውን ህልምን ለማሳካት እና እፎይ ለማለት ቢጓዙም ሌላ የመገፋት መከራ ደግሞ ገና የብስ በረገጡ ማግስት ወደ ሀገራችሁ ልንጠርዛችሁ ነው የሚባለው ድምፅ ያስተጋባባቸዋል ። አብዛኛው ወንዶች እየተደበደቡ ሴቶች እየተደፈሩ የየመንን በረሃዎች አቋርጠው ወርቅ ይታፈሳል ወደ ተባለበት የቱጃሮች ሀገር ሳውዲ ዐረቢያ ቢገቡም መከራው ለቁጥር አታክቷል ። ለወህኒ ከማዳረግ አልፎ በጥይት እየተደበደቡ ደመ-ከልብ ሆነዋል። በደቡብ አፍሪቃም ከነ ህይወታቸው በእሳት ተቃጥለው ኢሰበዊ ድርጊት ተፈፅሞባቸዋል ።

ወያኔ ኢትዮጵያን ከመቆጣጠሩ በፊት በትጥቅ ትግሉ ወቅት “ጭቆና ካለ፣ ትግል ይኖራል የሚለውን መፈክር ማስተጋባት ልማዱ ነበረ ፡፡ ይህም አነጋገሩ ባለፈ ባገደመበት ስፍራ ሁሉ የትግል አንዱ መልክ ይህን መሳይ ነው በማለት ከሆስፒታል መድሀኒቶችን፣ ባንኮችንም በመስበር ገንዘብን በመመዝበር ወዘተ ፥ የደርግን ጭቆና ለማስውገድ ! በሚል ሽፋን በመሳሪያ የትጥቅ ትግል እዚህ ደርሷል። የኢትዮጵያ ህዝብም ከዚህ ሀገር ሰባሪ ድርጊት የሚማረው ምንም ነገር የለም ቢሆንም

ለወያኔ ቡድን በድጋሚ መፈክሩን ሊደግምለት፥ ሊያስታውሰው “ጭቆና ካለ፣ ትግል ይኖራል” በሚል ጉዞ ስለተንሰራፋው አንባገነናዊ አገዛዝ ዜጋው በአንድነት ሊታገለው የሚያስችል በቂ የሆነ መፈክሩን
ህዝብ እንደወረሰበት ወያኔ ሊያውቅ ይገባዋል። አሁንም እንላለን “ጭቆና ካለ፣ ትግል ይኖራል” ነገር ግን ትግሉ ኢትዮጵያውያን የሚተባበሩበት ህዝባዊ ትግል እንጂ የወያኒያን ጎጣዊ ትግል አይነት አይደለም።

አቧራዉ ከረገበ በኋላም ወያኔ በቤተ መንግስት ተኮፍሶ `` ደርብ ፥ እስስስስ እስስስስስ `` እያለ ነጠላ አሸርጦ ከበሮ ቢያነግት እና የጭፈራው ድምፅ የኢትዮጵያውያንን የለቅሶ ድምፅ ሊያሰማው ሳይችል ቢቀርም የገባበት በሩ ድረስ ጭቆናው ይብቃ! ጭቆናው ያብቃ! እያለ በቆራጥነት በተለያዩ ስፍራዎች ስለተገደሉት ንፁህ ኢትዮጵያዊ ስደተኞች የህይወት መጥፋት ህዝብ ድምፁን ለማሰማት በዛሬው እለት እየተመመ መሔዱ ወያኔ የህዝብን ትብብር የሚያጤንበት ሂደት እና በተለይም የወጣቱ ክንድ እንደሚያሰጋው የተብራራለት ሆኗል።

ይህንን የጥፋት ኃይል በህዝባዊ አመፅ ተባብረን ማስወገድ አለብን የሚለውን እውነተኛ አቋም የማይጋራ ዜጋም፤ ድርጅትም ያለ የለም። ካለም እርሱ ወያኔ ብቻ ነው።ከዚህ በመነሳትም ሁሉም ሀገር ወዳድ ትግሉን ከራሱ፣ ከቤተሰቡ፣ ከቀዬው ፣ ከባልጀራው በመጀመር ፥በቅርቡ ላሉት እያሳወቀ ፤ ለሃይማኖት ተቋማት መሪዎች የፖለቲካ ንቃታቸውን እየኮረኮረ በማነቃቃት የሃይማኖት ሰባኪያንም ለጉባኤያቸው እውነቱን በመናገር ስለ ህዝብ ነፃነት እና ፍትህ እንዲያስተምሩ እንዲሰብኩ እውነቱን እውነት ሀሰት የሆነውን ሀሰት ብለው ያለምንም መወሻከት በመጠቆም፣ በከተማ ሆነ በገጠር እና በየክፍለሃገሩ ተበታትነው ያሉ ሁሉ“ያልሰማህ ስማ፣ የሰማህ ላልሰማ አሰማ!” በሚል ታልቅ ድምፅ በድፍረት ያለምንም መጎናበስ በአደባባይ በየገጠር ክልሉ ፣ በወገናችሁ ላይ የሚታየውን ችግር እና በደል ለህዝብ እና ለዓለም ማሳወቅ የዜግነት ግዴታ ነው፡፡

ስለሆነም በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው ለ40 አመታት ያህል የደም ምድር አኬልዳማ! እየተባለ የተዜመውን ዜማ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ሰርዞ በሰላም እና በድል ዜማ ለመተካት በቅድሚያ የጋራ ግባችን፥ የወያኔን ስርዓት ማውደም ! የሚለው ሊሆን ሲችል ብቻ ፥ በየትኛውም ዓለም ተበታትነን የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ለህዝባዊ አመፁ ክንዳችንን እናነሳለን ማለት ነው። ልዩነት ፣መራራቅ፣ ጎሰኝነት እና ጎጠኝነት በሌለበት የተባበረ ክንድ ለውጥ ያመጣል።

ሕዝባዊ አመፅ በወያኔ ላይ ይፋፋም !!!